## በመጋቢት እና በሚያዝያ ወሮች መግቢያ፥ ፳፻፱ እና ፳፻፲፩ ዓመተ-ምሕረት፤

## በኢትዮጵያ ምድር እና በግብፅ አገር የደረሱት ዕልቂቶች

# መለኮታዊ መልእክት፡

## ምንድር ነው?

**ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡-**

፩ኛ፡ በኢትዮጵያዋ አዲስ አበባ መናገሻ ከተማ ክልል በምትገኘው፡ "ቆሼ" በምትባለው መንደር፡ በመጋቢት ፪ ቀን፥ ፳፻፱ ዓመተ-ምሕረት፤

፪ኛ፡ በግብፅ ምድር፡ በካይሮና በእስክንድርያ ከተማዎች፡ ሚያዝያ ፩ ቀን፤ ፳፻፱ ዓመተ-ምሕረት

፫ኛ፤ በኢትዮጵያ፡ የጌታ ምጽአት በሚታሰብባት **"ደብረ-ዘይት"** የሚል ስያሜ ባላት፡ የቢሾፍቱ መንደር አቅራቢያ፡ በ፳፻፱ ዓ.ም. የቆሼው አደጋና ዕልቂት በተቃጣበት ተመሳሳይ ወርና ተቀራራቢ ቀን፡ በመጋቢት ፩ ቀን፥ ፳፻፲፩ ዓመተ-ምሕረት የደረሱትን ጥቃት እና ዕልቂት በሚመለከት፡ በኪዳነ-ምሕረቱ ጸጋና በረከት፡ ሙታኑ፡ ዕረፍተ-ነፍስን፥ ቋሚ ቤተሰቦቻቸውም፡ መጽናኛውን መንፈስ እንደሚያገኙ በማመንና በመተማመን፤ ከዚህ የሚከተለውን **መለኮታዊ መልእክት፡** ለቅዱሱ ኪዳን የኢትዮጵያ ልጆቿ ታስተላልፍ ዘንድ፡ አግባብ ኾኖ አግኝታዋለች።

፩ኛ. በዓለም ላይ ሠፍረው በሚገኙት የሕዝቦቿና የአሕዛቧ ኅብረተ-ሰብ መካከል፡ በድንገተኛ አደጋ ረገድ፡ እስከዛሬ ሲሰማ የተኖረው የዕልቂት መርዶ፡ የመሬት መደርመስ፤ ወይም፡ የሕንፃ መደርባት፤ ከዚያም ቢያልፍ፡ የእሳተ ገሞራ ፍንዳታንና የሰደድ እሳትን፤ የዝናብ ውሽንፍርንና የውኃ ጎርፍን፥ ወይም፡ የዐውሎ-ነፋስንና የማዕበል ማጥለቅለቅን፥ ደግሞም፡ የመሬት ነውጥንና የበረዶ ፍልሰትን በመሰሉ፤ በተፈጥሮ ኃይላት ምክንያት የሚደርሱ፤ ድንገተኛ አደጋዎች ያስከተሉ የጥፋት ዓይነቶች ብቻ ነበር።

**ዛሬ ግን፡ ሰዎች፡ "ራሳቸው የከመሩት ቍሻሻ ተደርምሶ፥ ወይም ተደርብቶ፡ በመቶዎች በሚቆጠሩ ሰዎች ላይ፡ የሞትና የአካል ጉዳትን አስከተለ!" የሚል አሳዛኝና አሳፋሪ ወሬ፡ ለመጀመሪያ ጊዜ ተሰማ።**

ይህ የተለየ ጉድ ነገር፡ ለምን፡ "ኢትዮጵያ" ተብላ በምትታወቀው፡ በቅዱስ ኪዳኗ አገር፡ መናገሻ ከተማ በኾነችው፡ በአዲስ-አበባዋ አንዲት መንደር ደርሶ ታየ? በጊዜውስ ረገድ፡ ለምን፡ ይህ፡ የአኹኑ ዘመን ወቅት፡ ለዚህ ጉደኛ እንቆቅልሽ ተመረጠ?

፪ኛም. በኹለት አብያተ-ክርስቲያናቸው ውስጥ ተሰባስበው፡ በዓለ-ሆሣዕናን በማክበር ላይ በነበሩ፡ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ-ክርስቲያን የበላይ መሪዎች በኾኑ፣ የግብፅ ኦርቶዶክሳውያንና ኦርቶዶክሳውያት ዜጎች መካከል፡ ለቅጣት መሣሪያነት በተመረጡ፡ **በአንድ የእስልምና አክራሪ ሽማቂና በአንድ ሌላ የአጥፍቶ ጠፊ ገዳይ ፍንዳታዎች፡ በመቶዎች በሚቆጠሩ ሰዎች ላይ የሞትና የአካል ጉዳትን ያስከተለ፡ *አሠቃቂና አስደንጋጭ የኾነ ጥቃት ደርሶ ታየ።***

ይህኛውም ጥቃት ለምን ደረሰ? ለዚህ ጥያቄ፣ ለቀደመውም፡ ተገቢውን ምክንያታዊ መልስ ለመስጠት፡ የቅዱሱ ኪዳን አማኝ ለኾነ ኢትዮጵያዊ ሰውነት፡ የሚያዳግተው አይደለም፤ መልሱ፡ ግልጽ ነውና።

እንግዴህ፡ ከዚህ ስለቀደመው፡ የኢትዮጵያን ሰዎች ስለሚመለከተው፡ ስለቶሼ ጥያቄ፡ የሚሰጠውን መልስ፡ ወደኋላ በማቆየት፡ ለዚህኛው፡ ለኹለተኛው፥ የግብፅ ሰዎችን ለሚመለከተው፡ ለቅርቡ ጥያቄ፡ የሚሰጠው መልስ፡ እንደሚከተለው ይኾናል። አዎን! ከአንድ ሳምንት በፊት፡ ቀደም ብላ ከነበረችው ዕለተ-ሰንበት ማግሥት በዋለችው፣ በመጋቢት ፳፫ ቀን፥ ፳፻፱ ዓመተ-ምሕረቷ ዕለተ-እሑድ፡ ሊከበር የሚገባውን፡ በዓለ-ሆሣዕና፡ የግብፅ ኦርቶዶክሶች፡ "ከመለኮታዊው ሥርዓት ውጪ፣ መለኮታዊውንም ዐዋጅ በመተላለፍ፡ ለዝንተ-ዓለም፡ ሲያደርጉት እንደኖሩት ኹሉ፡ አኹንም፡ አላገባብ፣ በማናለብኝነት፡ በሚያዝያ ፩ ቀን፥ ፳፻፱ ዓመተ-ምሕረት በዋለው፡ በትንሣኤው በዓለ ዕለተ እሑድ፣ በማክበራቸው ይኾናል!" ብሎ፡ በመንፈሳዊውና በሃይማኖታዊው የዕውቀት ብቅዓት ማስረዳቱ ያስኬዳል።

ይህን የመሰለው ጥቃትና ዕልቂት፡ በበለጠ እየጨመረ ኼዶ፡ ሊፈጸም የበቃው እኮ፡ የኢትዮጵያ የቃል ኪዳን አምላክ የኾነው፣ የእግዚአብሔር አብ እና የእግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያም ልጅ፡ እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕ፡
የኪዳነ-ምሕረቱ ዘመን በሰፈነበት፡ በአኹኑ ጊዜ በመኾኑ፡ "ይህ ሊኾን፡ እንዴት ቻለ? ለምንስ ተፈቀደ?" የሚለውን ጥያቄ፡ ሊያስነሣ የሚያስገድድ ኾኗል።

በዚህ የኪዳነ-ምሕረቱ ዘመንማ፡ ሊኾን፣ ሊደርስም የሚገባው፡ ይህ አልነበረም። ምክንያቱም፡ ከኪዳነ-ምሕረቱ ጋር፡ እንዲህ የሚል፡ መለኮታዊ ቃል-ኪዳን ስላለ ነው። ይኸውም፡- "**አኮኑ፡ ክልኤቲ አዕዋፍ ይሠየጣ፡ በክልኤ ጸሪቀ አሶርዮን? ወአሐቲ እምኔሆን፡ ኢትወድቅ ውስተ ምድር፣ ዘእንበለ ያእምር አቡክሙ ሰማያዊ። <u>ወለክሙሰ፡ ሥዕርተ-ርእስክሙኒ ኵሉ፡ ኍሉቅ ውእቱ።</u>**

"ኹለት ወፎች፡ በኹለት መሓለቅ የሚሸጡ አይደለምን? ነገር ግን፡ እያንዳንዳቸው፡ የሰማዩ አባታችሁ ሳያውቀውና ሳይፈቅድ፡ በምድር ላይ አይወድቁም። <u>የእናንተማ፡ የራስ ፀጉሮቻችሁ ኹሉ፡ እያንዳንዷ እንኳ ሳትቀር፡ በፈጣሪያችሁ ዘንድ፡ የተቆጠረችና የተጠበቀች ናት።"</u> የሚለው ነው።

ስለዚህ፡ ሊኾን፣ ሊደርስም የሚገባው፡ እንዲህ ተብሎ የተነገረውን፡ ይህን መለኮታዊ ቃል-ኪዳን የሚያጸና፡ የሕይወት ጥበቃና የደኅንነት ዋስትና እንጂ፣ በኢትዮጵያዋ አዲስ አበባ መናገሻ ከተማ ክልል በምትገኘው፡ "ቆሼ" በምትባለው መንደር፡ በመጋቢት ፪ ቀን፥ ፳፻፱ ዓመተ-ምሕረት፣ ፪ኛም፡ በግብፅ ምድር፡ በካይሮና በእስክንድርያ ከተማዎች፡ ሚያዝያ ፩ ቀን፣ ፳፻፱ ዓመተ-ምሕረት የደረሱትን ጥቃት እና ዕልቂት የመሰለውን፣ በበለጠ እየጨመረ ኼዶ፡ ሲፈጸም የሚታየውን፡ ይህን ዓይነቱን ጥቃትና ዕልቂት፡ አልነበረም። (ማቴ. ፲፥ ፴።)

## ለዚህ ተገቢ ጥያቄ፡

## የተሰጠው ትክክለኛው መልስ።

ለዚህ ለደረሰው ኹኔታ፡ ሰዎች፡ እጅግ ብዙዎች የኾኑ የተለያዩ ምክንያቶችንና ትችቶችን፡ ያለማቋረጥ በማቅረብ ላይ እንደሚገኙ ይደመጣል። ይኹን እንጂ፡ የእውነታው ቍም-ነገር፡ በትክክል ይህ አይደለም።

የእግዚአብሔር መንግሥት የኾነችው፡ የራሷ የኢትዮጵያና የልጆቿ፡ ፈጣሪዎችና ባለቤቶች፣ መሪዎችና አስተዳዳሪዎች፣ መጋቢዎችና ጠባቂዎች ከኾኑት፡ ከራሳቸው ከእግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያም እና ከልጇ ከወዳጇ፡ ከእግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕ፡ በመለኮታዊ መልእክትነት፡ በአጠቃላይ፡ ለዓለሙ ኅብረተ-ሰብ፣ በተለይም፡ "ኢትዮጵያዊ ነኝ!" ለሚለው፡ ለዚህ ትውልድ፡ በቀጥታ የሰጡት የእውነታው ቍም-ነገር የኾነው፡ ትክክለኛውና ግልጹ መልስ፡ እነሆ ይኼውላችሁ!

«እናንተ፡ በአጠቃላይ፡ የዓለሙ ኅብረተ-ሰብ የኾናችሁት፣ በተለይም፡ "ኢትዮጵያዊ ነኝ!" የምትለው ትውልድ፡ ይህ፡ አኹን የደረሰባችሁና ወደፊትም፡ ሊመጣባችሁ እየተዘጋጀላችሁ ያለው፡ የጥፋቱና የቅጣቱ ዕልቂት፡ እናንተን ሰዎችን ጨምሮ የሚያጠቃልለው፡ የዚህ ዓለም ፈጣሪና ባለቤት ከኾነው፡ ከእግዚአብሔር አምላክ ታዝዞ፣ ወይም፡ የእርሱ ከኾነችው ከሥነ-ፍጥረት ሥርዓትም እንኳ፡ መንጭቶ የመጣባችሁና ወደፊትም የሚመጣባችሁ አይደለም።

«እንዲህ ካልኾነ፡ ታዲያ! እነዚህ፡ ፩ኛ፡ በኢትዮጵያዋ አዲስ አበባ መናገሻ ከተማ ክልል በምትገኘው፡ "ቆሼ" በምትባለው መንደር፡ በመጋቢት ፪ ቀን፥ ፳፻፱ ዓመተ-ምሕረት፣

«፪ኛ፡ በግብፅ ምድር፡ በካይሮና በእስክንድርያ ከተማዎች፡ ሚያዝያ ፩ ቀን፣ ፳፻፱ ዓመተ-ምሕረት የደረሱት ጥቃት እና ዕልቂት፡ "ከየት መጡ!" ሊባል ነው?

«መልሱ፡ "**እራሳችሁ፣ በእየራሳችሁ ዕውቀትና ብልጠት፣ ጥበብና ብልሃት፥ ክፋትና ተንኰል ያመጣችሁት ነው!**" የሚል ይኾናል። ይህ መልስ፡ እውነት መኾኑን፡ በትክክልና በገሃድ ትገነዘቡት ዘንድ፣ ከተከተላችሁት የተሳሳተው የአስተሳሰብና የተግባር አካኼዳችሁም፡ በንስሓ ትመለሱ ዘንድ፡ የተፈጥሮ ሥርዓት የኾነችው፡ **የእግዚአብሔር እውነት፡** ያቀረበችላችሁን ማስተማሪያና መምከሪያ፥ መገሠጫና የመጨረሻ ማስጠንቀቂያም፡ እስኪ፡ ለአንዴ አስተውሉት? እውነታውን ዐውቃችሁትና ተረድታችሁት፣ በመጨከን ትቀበሉት ዘንድ ደግሞ፡ በዚህ፡ ዕልቂት ውስጥ፡ የራሳችሁ የኾኑትና እናንተኑ የመሰሉት፡ ጥቂቶቹ ወገኖቻችሁ፡ ከመካከላችሁ ተውጣጥተው፡ እንዴት መሥዋዕት እንደኾኑላችሁም ተመልከቱት?!

«አዎን! በግብፅ ምድር፡ ባለማቋረጥ እየተሰማ ያለውን ዋይታ፡ ማዳመጣችሁን የምትቀጥሉበት ኹኖ፣ እስኪ፣ በኢትዮጵያ የኾነውን፡ የቆሼን ነገር፡ እንደምሳሌ አድርጋችሁ ወስዳችሁ፡ በመንፈሳዊ የአስተሳሰብ ጥልቀት አጢኑት!

«ለመኾኑ፡ ያ፡ የቆሻሻ ክምር፡ የማን ነው? ማነው የፈጠረው? የተፈጠረው እኮ፡ በእናንተው ነው? እኛ አልፈጠርነውም፤ ሥነ-ፍጥረታችንም እንኳ አላዘጋጀችውም።

«እናንተው፣ በእየቤታችሁ ሠርታችሁ ካወጣችሁት፥ ከእየባዕዳኑ የማምረቻና የንግድ ድርጅቶችም ያስገኛችሁት፥ 'ቍሻሻ" ነው ብላችሁም፡ የሰበሰባችሁትና የከመራችሁት አይደለምን? አዎን! ነው እኮ!

«ታዲያ! ይኼ ድርጊታችሁ፡ የእናንተኑ ማንነትና ምንነት፡ መልሶ፣ እንደመስታዋት አንጸባርቆና ቍልጭ አድርጎ፣ እንደተራራም አቁሞ፡ ለእየራሳችሁና ለመላው ፍጥረተ-ዓለም፡ አረጋግጦ ያሳየና አጋልጦ የመሰከረባችሁ መኾኑ፡ ሊታበል፡ ከቶ ይቻላልን? አይቻልም።

«በቆሻሻው ክምር የተመሰለውን ጠንቀኛ ክፋታችሁን፡ ራሳችሁ፡ ተራራና ገደል እስኪኾን ድረስ፡ እንደሕንፃ መሥርታችሁትና እንደግድግዳ አቁማችሁት፣ እንደጣሪያም ደምድማችሁት፣ ከሠራችሁት በኋላ፡ ያው ሥራችሁ፡ መልሶ፡ ራሳችሁን እንዳጠፋ፡ እየራሳችሁ፡ በየዓይናችሁ ብረት፡ ተመለከታችሁት አይደለምን? አዎን! ይኸው አያችሁት፣ ተመለከታችሁትም እኮ!

«እንደዚሁም ኹሉ፣ አዎን! እውነተኛውንና ተፈጥሮአዊ፥ እግዚአብሔራዊም የኾነውን፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነታችሁን ነቅፋችሁትና ንቃችሁት፣ ጠልታችሁትና ወርውራችሁት፣ ጥላችሁትና ትታችሁት፡ ከቅድስናችሁ ይልቅ፡ እናንተ፡"ቆሻሻ" የምትሉትን ርኩሰትን፣ የእናንተ ያልኾነውን የባዕዳኑን፥ የዓለሙንና የሥጋ ብቻ የኾነውን፡ ሰውኛውንና ሰይጣናዊዉን በመምረጣችሁ፣ በዚሁ፡ በያዛችሁት ሥጋዊና ዓለማዊ፣ ሰብአዊና ሰይጣናዊ ህልውናችሁና ሕይወታችሁ እንኳ፡ እንግዴህ ወዲህ፡ የሚጠብቃችሁ ዕድልና ጽዋ፡ ከቶ ምን ይመስላችኋል?

«የሚጠብቃችሁ ዕድልና ጽዋማ፡ በአንድ በኩል፡ በቆሼ ተራራ የደረሰውን የመሰለ ድንገተኛ ዕልቂት፣ በሌላው በኩል ደግሞ፡ የእግዚአብሔርን ሥርዓት፡ ራሳቸው አፍርሰው፡ "የእግዚአብሔርና የኢትዮጵያ የቃል ኪዳን ልጆች" የተባሉትን ኢትዮጵያውያንንና ኢትዮጵያውያትን፡ እንደእነርሱ ላለው፡ ለአምልኮ ሥርዓተ-አልበኝነት በዳረጉት፡ በግብፅ ኦርቶዶክሳውያንና ኦርቶዶክሳውያት ላይ፡ ያለማቋረጥ እየወረደ ያለው የቍጣ መቅሠፍት ይኾናል።

«እንግዴህ፡ በምድር ላይ፣ በዓለሙም ኹሉ ያለው፡ የትኛው፡ የምትተማመኑት፡ የሰዎች ኾነ፣ የሰይጣናት መንግሥት ነው፡ ከሚመጣው የዕልቂትና የቍጣ መቅሠፍት፡ ሠውሮና ታድጎ ሊያድናችሁ የሚቻለው? ማንም የለም።

«አዎን! የ፯ሺ፭፻፱ ዓመታት ዕድሜ ወዳለው፡ ወደቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ተዋሕዶ ሃይማኖታችሁና ምግባራችሁ፣ ሥርዓታችሁና ማንነታችሁ፡ እያንዳንዳችሁ፡ በነፍስ፥ ወከፍ፣ እየራሳችሁን፡ በእውነተኛ ንስሓ፡ በምትመልሱባት ቅጽበት፡ በኪዳናዊ አባትነታችንና እናትነታችን፣ የፍጹሙ-ምሥዋዕ መድኃኒትነታችንና የሰላመ-መስቀል ቤዛነታችን ካዳንናችሁ፡ ከእኛ፡ ከፈጣሪያችሁ በቀር፡ ከሚመጣው የዕልቂትና የቍጣ መቅሠፍት፡ ሠውሮና ታድጎ ሊያድናችሁ የሚቻለው፡ ማንም የለም።

«ይህ እውነታ፡ በቅዱሱ ኪዳን፡ የቃል-ኪዳን ፈጣሪያችሁ ብቻ ሳንኾን፡ የሰማዩ አባታችሁ እና የሰማይዋ እናታችሁ፣ መድኃኒታችሁና ሰላማችሁ፣ ምሥዋዕናችሁና ቤዛችሁ፥ ወንድማችሁና እኅታችሁ፥ ጓደኛችሁና ባልደረባችሁ የኾንነውን፡ እኛን፡ እግዚአብሔር ጸባዖት አብንና እግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያምን፣ እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕንና እግዚአብሔር መንፈስ-ቅዱስን፡ በቤተ-ሕዝብነታችሁና በቤተ-ምልክናነታችሁ፥ በቤተ-ክህነትነታችሁም ሳይቀር፡ በገሃድ ክዳችሁ፣ በመንግሥታችንም ላይ፡ በይፋ ዓምፃችሁ፡ የአምልኮ አመንዝራነታችሁን፡ በዐዋጅ ስለፈጸማችሁ፡ ለሚጠብቃችሁ የጥፋት ዕልቂት፡ ምክንያቶቹ፡ እየራሳችሁ እንጂ፡ ሌላ ማንም አለመኾኑ፡ ያለውልውልና ያለጥርጥር የሚያመላክታችሁ በቂ ማስረጃችሁ ኾኖ ቀርቦላችኋል።»

## የዚህ እውነታ መጠናከሪያ።

ይህ እውነታ፡ በዚህ ማስረጃነቱ ብቻ ሳይወሰን፡ በቅርቡም፣ በሩቁም፡ ሲደርሱ ከኖሩት፡ ከሌሎቹ የዕልቂት መከራዎች ጋር፡ እነዚህን፡ በኢትዮጵያም፥ በግብፅም የደረሱትን፡ የዛሬዎቹን፡ እውን ኹኔታዎች፡ አገናዝባችሁ ስትመለከቷቸው፡ የብዙዎች ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፣ ግብፃውያንና ግብፃውያት ሕይወት በተሠዋባቸው፡ በእነዚህ አሠቃቂ ጥቃቶችና ዕልቂቶች፡ እግዚአብሔር፡ የዓለሙን ትውልድ ለሚወክሉት፡ ለዛሬዎቹ የየአህጉራቱ ሕዝቦች፥ ይልቁንም፡ ድንግል ማርያምን ለምትወክለው ለኢትዮጵያ፡ "ሕዝቧም፥ ልጆቿም ነን!" ለምትሉት፡ ለእናንተ፡ የዘመኑ ትውልድ አባሎች፡ መልእክቱ፡ ከቶ ምንድር ይመስላችኋል?

ወይስ፡ ይህ ኹሉ፡ ለምን እንደኾነ የሚያውቀው፡ እርሱው፡ ፈጣሪያችንና ሰላማችን፡ ኢየሱስ መሲሕ፡ ዛሬም፡ በመንፈስ ቅዱስ፡ እንዲህ እያለ የሚናገረንን ቃሉን፡ "አንሰማህም!" ብለን፡ ንቀንና አቃልለን፥ ቸል ብለንና እንዳልሰማም ኾነን፡ ዝም ብለን አልፈነው፡ ልንኼድ ይገባናልን?

ይህ ቃሉም፡ እንዲህ ተብሎና ተጽፎ፡ እየተነበበ ሲደመጥ የተኖረው ነው፡-

**"ወበውእቱ መዋዕል፡ መጽኡ ሰብእ ኀቤሁ፤ ወዜነውዎ፡ በእንተ ገሊላውያን፣ እለ ደመረ ጲላጦስ ደሞሙ፣ ምስለ መሥዋዕቶሙ።**

"በዚያ ወራት፡ ሰዎች፡ ወደፈጣሪያችንና ሰላማችን ኢየሱስ መሲሕ መጥተው፡ [በዚያን ጊዜ፡] ጲላጦስ፡ ደማቸውን፡ ከመሥዋዕታቸው ጋር ስለቀላቀለው፤ ስለገሊላ ሰዎች፥ *[በአኹኑ ጊዜም፡ በኢትዮጵያ አገር፡ በአዲስ አበባዋ የቆሼ መንደርና የደብረ-ዘይት አቅራቢያ ከተማ፥ እንዲሁም፡ በግብፅ ምድር፡ በካይሮ አቅራቢያና በእስክንድርያ ከተማዎች ላይ ስለደረሰው የሰዎች ጥቃትና ዕልቂት]* ነገሩት።

**"ወአውሥአ እግዚእ ኢየሱስ፤ ወይቤሎሙ፡- 'ይመስለክሙኑ፡ እሙንቱ ገሊላውያን፡ ኃጥኣን፡ እምኵሉ ሰብአ ገሊላ፡ እስመ ዛቲ ሕማም ረከበቶሙ? አልቦ፣ እብለክሙ! እመሰ ኢነሳሕክሙ፡ አንትሙኒ፡ ከማሆሙ ትትሓጐሉ ኵልክሙ።**

"እርሱም መልሶ እንዲህ አላቸው፡- 'ይህች መከራ ስላገኘቻቸው፡ እነዚህ ገሊላውያን *[በአኹኑ ጊዜም፡ በኢትዮጵያ አገር፡ በአዲስ አበባዋ የቆሼ መንደርና የደብረ-ዘይት አቅራቢያ ከተማ፥ እንዲሁም፡ በግብፅ ምድር፡ በካይሮ አቅራቢያና በእስክንድርያ ከተማዎች፡ ጥቃትና ዕልቂት የደረሰባቸው፡ የኢትዮጵያ እና የግብፅ ሰዎች]*፡ ከቀሩት፡ የገሊላ *[የኢትዮጵያ እና የግብፅ፥ የሌሎችም ሀገሮች]* ሰዎች ኹሉ ይልቅ ተለይተው፡ ኃጢአተኞች የኾኑ ይመስላችኋልን? አይደለም፤ እላችኋለሁ! እናንተም፡ ንስሓ ካልገባችሁ፡ ኹላችሁ፡ እንደእነርሱ ትጠፋላችሁ።

**“'ወይመስለክሙኑ፡ እሉ ዐሠርቱ ወሰመንቱ፡ እለ ወድቀ ላዕሌሆሙ ማኅፈድ፡ በሰሊሆም፣ ወቀተሎሙ፣ ከመ እሙንቱ ኃጥአን፡ እምኵሉ ሰብአ ኢየሩሳሌም? አልቦ፣ እብለክሙ! እመሰ ኢነሳሕክሙ ከማሆሙ፣ ትትሐጐሉ አንትሙኒ ኵልክሙ።**

"ወይስ፡ እነዚያ፡ በሰሊሆም፡ ግንብ ተጭኖ የገደላቸው፡ ዐሥራ ስምንቱ *[መቶ አምሳ-ሰባቱ፡ የኢትዮጵያ፡ በቆሼ መንደር፣ መቶ አምሳ-ሰባቱ፡ የኢትዮጵያ፡ በደብረ-ዘይት ከተማ አቅራቢያ እና አርባ ዘጠኙ፡ የግብፅ]* ሰዎች፡ ከቀሩት፡ የኢየሩሳሌም *[የኢትዮጵያ እና የግብፅ፥ የሌሎችም ሀገሮች]* ሰዎች ይልቅ ተለይተው፡ ኃጢአተኞች የኾኑ ይመስላችኋልን? አይደለም፤ እላችኋለሁ! እናንተም፡ ንስሓ ካልገባችሁ፡ ኹላችሁ፡ እንደእነርሱ ትጠፋላችሁ።”

ታዲያ! እኛ ኹላችን፡ ኪዳናውያት እና ኪዳናውያን፡ እንዲህ የሚለንን መለኮታዊ መመሪያ ቃል ሰምተን ፈጽመናልን? ወይስ፡ ለመፈጸም፡ ገና እያመነታንና እየወላወልን ነን? (ሉቃ. ፲፫፥ ፩-፭።)

ወይስ፡ “እናምንብሃለን!” ብለን፡ በስሙ ተጠምቀንና ተጠርተን ለምንከተለው፡ የዓለም ክርስቲያኖች ኹሉ፥ በተለይም፡ እየራሳችንን፡ “ኢትዮጵያዊ/ ኢትዮጵያዊት” ብለን፡ ለፍጥረተ ዓለሙ ላስተዋወቅነው ኪዳናውያን እና ኪዳናውያት ኹሉ፡ ዲያብሎስ፡ ከሽህ ዓመት እሥራቱ፡ ለጥቂት ጊዜ ከተፈታ በኋላ ስለሚኾነው፡ ስለዓለሙ ፍጻሜና ስለኢየሱስ መሲሕ ዳግም ምጽአት፡ ይኸው መሪያችን ኢየሱስ መሲሕ፡ ያ፡ በቃሉ የነገረንና በራእየ ዮሓንስ ያመለከተን፡ “የእግዚአብሔር ቀን” እየደረሰ ስለመኾኑ፡ ገሃድ የኾነ የማስጠንቀቂያ ምልክትን መስጠቱ ይኾን? ወይስ፡ 'ምንን እያመለከተን ነው?' ብለን፡ እየራሳችንን በተመስጦ መጠየቅ የሚያስፈልገን መኾኑን፡ በዚህ አጋጣሚ፡ ኹላችሁንም ልናስታውሳችሁ እንወድዳለን።

እንግዴህ፡ የአምላክ እናት በኾነችው፡ በኢትዮጵያዋ እግዝእተሔር እም፡ድንግል ማርያም፡ የእግዚአብሔር መንግሥትነት፡ እስካኹንና ዛሬ፥ ወደፊትም፡ ለዘለዓለም የምንኖርበትን፡ ይህን፡ የቅዱሱን ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ተዋሕዶ ሃይማኖታችንን በማጽናት፡ በምግባራችን እንጠናከር ዘንድ፡ ይህን መልእክቱን፡ በመንፈስ ቅዱስ ተረድተንና በማስተዋል ተመልክተን፡ የሚገባንን እንድንፈጽም፡ ዕድሉንና ችሎታውን ለሰጠን እግዚአብሔርና ለቅድስት እናቱ፡ ድንግል ማርያም፡ የማያቋርጥ ምስጋናችንን፡ በያለንበት እናቀርባለን።